የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ–የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 34
ADDIS ABABA - 9th Febraury 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፬/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
ለመሠረተ ጤና አገልግሎት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፱፻፸፱

## CONTENTS

Proclamation No. 154/1999
African Development Fund Loan Agreement for financing the Primary Health Care Services Project Ratification Proclamation ........................ Page 979

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፬/፲፱፻፺፩
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመሠረተ ጤና አገልግሎት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ዩ.ኤ. ፳፱ሚሊዮን ፮፻፸ሺ (ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ «ለመሠረተ ጤና አገልግሎት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፬ /፲፱፻፺፩» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 154/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development fund stipulating 'that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of UA 29,670,000 (twenty nine million six hundred seventy thousand Units of Account) for financing the Primary Health Care Services Project, was signed in Abidjan on the 17th day of December, 1998;

WHEREAS , basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS ,the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 9th day of February, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for financing the Primary Health Care Services Project Ratification Proclamation No. 154/1999."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ «የብድር ስምምነት» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢቲኤች/ፒአርአይ–ኤችኢኤ ፺፰/፵፪ የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ.ኤ. ፳፱ ሚሊዮን ፮፻፸ሺ (ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፣ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No.F/ETH/PRI-HEA/ 98/42, signed in Abidjan on the 17th day of December, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minster of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the loan amount of UA 29,670,000 (twenty nine million six hundred seventy thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 9th day of February, 1999.

Done at Addis Ababa, this 9th day of Febraury, 1999.

NEGASO GIDADA (DR)
PRESDIENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE